# የኢትዮድያ ህዝብ እንዲያውቀው

## ከኣስገደ ገ/ስላሴ

### የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ምን ይዞ እንዴትስ ሊመጣ ይችላል?

በኣገራችን ልማት ብልፅግና ሊመጣ፤ስራ አጥነት ጠፍቶ ሁሉም ዜጋ በየሙያውና በየኣቅሙ ሰርቶ ንሮውን የሚገፋበት ኣይጠላም፡፡በተጨማሪ ኣገራችን ኢትህዮድያ መልካም ኣስተዳደር ፣ፍትህና የህግ በላይነት፣እኩልነት የነገሰባት የበለፀገችና የለማች ኣገር እንድትሆነ ይፈለጋል፡፡እንዲሁም ህዝባችን ወደ ስደት መበታተን ቀርቶ ስራ ኣግኝቶ በኣገሩ የሞቀ ኑሮ ሊያሳልፍ ይፈልጋል፡፡በዘር በብሄር በወረዳና ኣውራጃ ክልለ መከፋፈል ቀርቶ ሁሉም ዜጎች በመላው የኣገራችን ቦታዎች እንደልባቸው እየዞሩ ሊሰሩ ሊነግዱና ኢንቨስተ ቢያደርጉ ለህዝብም ለኣገርም ለመንግስትም በጣም ጠቃሚ ነበር፡፡

በኣገራችን ባሉት ፖለቲካዊ ድርጅቶች እጅ የሚገኝ በኣስር ቢሌኖች የሚቆጠር ገንዘብ ወደ ድህነት መጥፍያ ፕሮጀክቶች ኢንቨስት ቢሆኑ የኣገራችን ባለሃብቶች በንፁህ ገንዘባችው ከሙስና የፀዳ በቅንነትና ታማኝነት ገንዘባቸውና ሙያቸው ወደ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ስራ በሚፈጥርና ድህነት በሚያጠፋ መንገድ በሚያሰማሩት ኣገራችን የበለፀገችና የለማች ሰላማዊና ፍትሕ የነገሰባት ከሆነች የኔም የህዝብም ፍላጎታችን ከላይ የተዘረዘሩት ናችው፡፡

በተጨባጭ በኣገራችን ያለ ችግር ግን የሚቀጥለው ይሆናል፡፡ወደ ኣሁን ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ከመግባቴ ግን ከኢህኣዴግ መንግስት በፊት የነበሩ ስርኣቶች መንደርደርያ ሃሳብ እንዲሆነኝ ጠቃቅሼ ልለፍ፡፡

1.በዘመነ ኣፄ ሃይለስላሴ ስርኣት የነበረ ችግር በዛ ስርኣት ሁሉም ኣይነት መብት ለዘውዳዊ ኣገዛዝ ዝርዝራቸውና የነሱ መዋቅር ላሁኑ የክልል፣የኣውራጃ፣ ወረዳ ምስሌነ የቀበሌ ዳኛና ሹመኛ፤የጎበዝ ኣለቃዎች የተመቸች ለብዙሃኑ ስቃይ ነበረች፡፡ለዚሁ መገለጫ የሚሆነው ተምህርት ህክምና ለገዢዎች ካልሆነ ለብዙሃን እድል የማይሰጥ በድርቅ ግዜ ትሎችና ሌሎች ሲመታ ህዝቡ ይድረስልኝ ጭህት ሲያሰማ የሚደርስለት ባልነበረበት መልካም ኣስተዳደር  ፍትህ የህግ በላይነት ተጠያቂነት ግልፅነት ለሽታም ኣልነበረም፡፡

ያ ዘመን ዘውዳዊ ኣገዛዙና ዘርዘራቸው ከነመዋቅራቸው የሚያጌጡበት ድሃው የሚበታተንበት ግዜ እያለ ለ40 ኣመት በህዝብ ጫንቃ ተጭነው ቆይተው በህዝብ ትግል ኣወዳድቃቸው ሳያምርባቸው ቀርቶ ተዋርደው ተበታተኑ፡፡

2.የደርግ ስርኣትም ከኣፄው ስርኣት የባሰ ሂትለራዊ በሆነ ኣፈና መግደል የህዝብ ንብረት መዝርፍና ማውደም ዜጎች ለ17 ኣመት ተሰቃይተው እንዲኖሩ ያደረገ በኢትዮድያ ህዝብ ዘግናኝ የሆነ እርምጃ በመውሰድ ዘር ያጠፋና በኣገራችን የህዝቦች ብሄር ብሄረሰቦች

በውስጣቸውዘረኝነትእንዲፈጠር ያደረገና በአገራችን ሊጠፋ የማይችል ለምጥ ፈጥሮ ያለፈ ነበር፡፡ደርግም ለ17 አመት የአገራችን ህዝብ ካፈነና፣ ካሰቃየ፣ካወደመ በኋላ በህዝቦች ጠንካራና ደማዊ ውግያ ውርደት በተሞላበት ወደቀ፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ስርአቶች የሚያመሳስላቸው፦

1.በሁሉም ስርአቶች በድርቅና በትል ህዝቡ ሲጎዳ ስለህዝቡ አይቸገሩም

2.መልካም አስተዳደር ፍትህ ይህግ የበላይነት ነፃነት አልነበራቸውም

3.የህዝብ ድምፅ የማይሰማበት ፤ሁሉም አይነት መልካም አስተዳደር ያልነበረበት

4.በሁለቱም ስርአቶች ሙስናና ወገናውነት አድልዎ ነበረ

5.ማህበራዊ አገልግሎት ለምሳሌ ዉሃ፣መብራት፣ህክምና፣ትምህርት ያልነበረበት

6.በህዝብ የተመረጡ መንግስት አልነበሩም

7.ለህብረተሰቡ ሊቀይሩ የሚችሉ የልማት ድርጅቶች ማስፋፋት አልነበረም

8.የአገራችን ሀብት እየተቦረቦረ ፤ጥሬ እቃው እየተሸጠ በውጭ ባንኮች ያስቀምጡት ነበሩ

9.ህዝቡ ስርአቶቹ በፈጠሩበት ቀውስ ወደ ጎረቤት አገሮች ለስደት ተዳርጎ ተበታትኖ ቀርቷል

10.በሁለቱም ስርአቶች በድህነት ምክንያት የኢትዮጵያ ሴቶች እንደአሁኑ ባይበዛም በሴተኛ አዳሪነት ስራ ተሰማርተው ነብሳቸው ሸጠው የሚኖሩ ሴቶች እጅግ ብዙ ናቸው፡፡

ያለፉት ስርአቶች ካየን በኋላ ወደ ህወሓት ኢህአዴግ የሚመራው መንግስት ስንመጣስ ምን ይመስላል?

ድህነትና ስደት በኢትዮጵያ በተለይ በአሁኑ ግዜ የእድገትና ትራንስፎረሜሽን እቅድ እናሳካለን የሚባልበት ግዜ በሁሉም ክልሎች ከትግራይ ጎንደር ጎጃም ወሎ ኦሮሞ ሸዋ ደቡብ ሶማል ጋንቤላ ወዘተ.በሚልዮኖች የሚቆጠሩ እድምያቸው ከ13 እስከ 45 ኣመት የሆኑ ወጣቶች ወንዶች ሴቶች ወደ ጅቡቲ፣የመን፣ኬንያ፣ሱዳን፣እስራኤል፣ዩጋንዳ፣ደቡብ አፍሪካ ተሰድደው የስደተኛ ክብርእንኳን ያላገኙ በየእስርቤቱ እየተሰቃዩ የሚገኙ ወደ ኣውሮፓና አረብ አገሮች ባህር ኣቋርጠውሲሸገሩ በጀልባ ተገልብጠው አሳ የዋጣቸው ብዙ ናቸው፡፡የሚሰደደው የሰው አይነት ወንድናሴትሳይለይ ከ8ኛ ክፍል እስከ ዲግሪ ምሩቃኖች የገጠር ገበሬዎች ነጋዴዎች ናቸው፡፡

የተከበራችሁ አንባብያን ይህ ስደት በኢትዮጵያ የሚል አጀንዳ መገለጫው በሁሉ ኢትዮጵያ ተመሳሳይ ቢሆንም በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ለመግለፅ ሰፊ ጥናት ስለሚያስፈልገው አሁን በዝርዝር የማቀርበው በትግራይና አከባቢዋን ያለ ነው፡፡

በትግራይ ስደትና ድህነት ባለፉት ስርአቶች ታይቶ የሚያውቅና ጭራሽ ህብረተሰቡን የሚያበታትንና ዘርም የሚያጠፋ ነው፡፡ምክንይቱም በአሁኑ ግዜ በትግራይ ገጠሮች ከ40 ኣመት እድሜ በታች የሚታረስ መሬት ስለሌለው ሌላ ቀርቶ ቤት ሰርቶ የሚተኛበት ለመኖር የማይችልበት ስለሆነ ህዝብ እንደህዝብ ወደ ሱዳን፣ኬንያ፣ጅቡቲ፣እስራኤል እየተሰደደ ነው፡፡

ሌላ የትግራይ ህዝብ ወደ ስደት የሚፈልስበት ምክንያት በክልላችን በህወሓት ማ/ኮሚቴ የሚመራ የትግራይ እርዳታ ማህበር ያቋቋመው ደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም የሚባል አበዳሪ ድርጅት ጥናት በጎደለው ከመቶ 18% ወለድ ለመክፈል ያበደረው ፤ከስሮ የሚከፍልበት አጥቶ አልከፈለም ሲል የቤት እንስሳ ፤የማሳው እህል ስለሚወረስ ተስፋ ቆርጦ ወደ ስደት ፈረሰ፡፡

በከተማ የሚኖር ወጣትም ትምህርት የጨረሰ ይሁን ያልጨረሰ የሚሰራበት የስራ መስክ ስለሌለ ተስፋ ቆርጦ የጨለማ ኑሮ ስደት መርጦ ወደ ስደት እየፈረሰ ነው፡፡ያ በከተማ የቀረውም በየኮፊሃውስና ዲኤስቲቪ ፊልም በጫት ቤት በድራግና ሌሎች ተጠምዶ ደንዝዞ ይገኛል፡፡በትግራይ የሴት ኣዳሪነት ስራ እንደ ትልቅ የፋብሪካ ስራ ሆነዋል ፡፡በትግራይ በሁሉም ትላልቅና አነስተኛ ከተሞች በአስር ሺ የሚቆጠሩ ቡና ቤቶችና ኮፊሃውሶች አሉ፡፡

እነዚህ ቡና ቤቶችና ኮፊሃውስ የሚገኙ ሴቶች በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣት ሴቶች አሉ፡፡በትግራይ ከህሞራ እስከ ኣላማጣ ከመቶዎች በላይ ሴተኛ ኣዳሪዎች አሉ፡፡ይህ በትግራይ

ያለው ድህነት ምን ደረጃ እንዳለ ኣንድ መገለጫ ነው፡፡ፑልሃውስ፣ ከረንቡላ በክልላችን ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ናቸው፡፡በነዚህ ፑል ቤቶች ስራ ያጡ ወጣቶች የሚሰበሰቧቸው ናቸው፡፡ከነዚህ ቦታዎች እንደሽሻና ድራግ ጫትም ኣብረው የሚሄዱ ናቸው፡፡የክልላችን መንግስት በጥቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት የሚቆጥራቸው ኮፊሃውስ መጠጥ ቤቶች ፑልና ከረንቡላ ቤቶች ናቸው፡፡
በትግራይ ክልል ኮንስትራክሽን የምይዘው የነበረ የቀን ሰራተኛ፣ኣናጢ፣ለሳኝ፣ግንበኛ ወዘተ.በኣሁኑ ግዜ ስራ ኣጢ ነው፡፡ምክንያቱም ሲሚንቶ መሰቦ ዋጋው ከፋብሪካው ዋጋ ሁለት እጥፍ ስለሚሸጥ ቤት ሰሪ መስራቱ ስላቋረጠ ድህነቱ እስከ ጠላ ፣ዳቦ፣እንጀራ የምትሸጥ ድሃ ሁናለች ማለት ነው፡፡
በትግራይ የኣፈርና ውሃ ጥበቃ ሊሰራ የሚችል ወጣት በኣገር ስለሌለ በየቀበሌው የሚኖሩ ገበሬዎች ሽማግሌዎች ስለሆኑ ክልሉ ያወጣው እቅድ በተፈለገው መንገድ ሊሳካለት ኣልቻለም፡፡
በትግራይ ልማት የሚባለው በሬድዮና ቴሌቪዥን የምንሰማው ባዶና ሃቅነት የሌለው ኣደንዛዥ እፅ ከመሆኑ ውጭ በተግባር የሌለ ነው፡፡ለሰው ልጅ ለመኖር ውሃ ነው ትልቋ ከተማችን መቀለ ሳይቀር 20 ኣመት ሙሉ በውሃ ጥም ተሰቃይቷል፡፡ውሃ ከሌለ ጤና የለም ውሃ ከሌለ ኮንስትራክሽን የሚባል ኣይታሰብም ፡፡በኣሁኑ ግዜ ኣድዋና ኣክሱም ካልሆነ የኣክሱምን ዘንድሮ ከኣድዋ ተስቦ ያገኙት በሌላ ቦታዎች በዉሃ እጦት ለብዙ በሽታ ተጋልጦ በስቃይ ይገኛል ታድያ ውሃ ሳትይዝ ልማት ይመጣል?የመንግስት ሰራተኛም በሁሉም መልኩ ደስተኛ ኣይደሉም ወገናውነት ኣድልዎ ሙስና የተጨማለቀ ቢሮክራሲ ስላለ ፍትህን ይፈልጋል፡፡ታድያ ህዝብ በስደት ከኣገር ውጭ ከተበታተነ ሙሁራኖች በስራ ኣጥነት በየኣደንዛዥ **ዕፆችና ስሶች ከተጠመዱ ፤የእድገትና ትራንስፎርሜሽን በየት ነው የሚመጣ?**

**ህወሓት ኢህኣዴግ የሚመራው መንግስት ከትግራይ ክልል ከሳምረና ግጀት ዓድግዶም ሌሎች ቦታዎች በድህነት ምክንይት ለልመናና ለስራ ወደ ኣዲስ ኣበባ ለተሰደዱ እንደህዝብ ለማኝ ብሎ በብዙሃን መገናኛ ተነግረዋል።እኔ በበኩሌ ልመና ጥሩ ኣይደለም መፍትሂ የሚሆነው ግን ለማኝ ብለህ ለህዝብ ከማዋረድ ስራ መፍጠርና መልካም ኣስትዳደር ማንገስ ነው።እነኚ የተሰደዱ ወረዳዎች ሃብታሞች እንደነበሩ ነው የማውቀው በትግል ወቅት ልጆቻቸው ንብረታቸው ገንዘባቸው ያለቁባቸው ናቸው።ልመና እኮ በኣሁኑ ግዜ ኣዲስ ኣበባ ያጥለቀለቃት ሳምረ ብቻ ኣይደለም ጎንደር፣ጎጃም፣ሰሜን ሸዋ፣ሌሎችም በልመና ተሰማርተዋል።እነዚህ ሰዎች የልመና ሱስ ስላላቸው ኣይደለም ዋና ችግራቸው መልካም ኣስተዳደር፣ፍትህ፣የህግ በላይነት፣ግልፅነትና ተጠያቂነት ስለሌለ ነው።በኣሁኑ ይቅርና ወደ ትላልቅ ከተሞች መሰደድ ለኢትዮጵያ በ360 ዲግሪ ወደ ከበቧት ኣገሮች እያቀና ነው።ይህ ደግሞ ለኣገራችን ትልቅ ኣደጋ ነው።**

**ኣንድ ኣንድ ሰዎች የሌላ ክልል ህዝብም ባለማወቃቸው የትግራይ ህዝብ እንደለማ ፍትህና መልካም ኣስተዳደር ተጠቃሚ እንደሆነ ይናገራሉ። ኣንድ ኣንድ ሙሁራንም የትግራይ ህዝብ ከሌላው ወንድሙ የኢትዮጵያ ህዝብ የበለጠ ኣልጋ በኣልጋ እንደሚኖር ይናገሩ ነበር።በመሬት ያለው ግን የትግራይ ህዝብ በጣም ድሃና ወደኋላ እየቆጠረ የሚሄድ ያለ ነው።ይህ ሲባል የትግራይ ህዝብ ኣይሰራም ማለት ኣይደለም ይሰራል ታታሪ ነው ግን መሪ ኣላገኘም።**

በሌላ በኩል የመሃል ኣገር ክልሎች ትግራይ በተለይ ለምታለች ብለው መናገራቸው እውነታቸው ነው።ይህ የሆነበት ምክንያት በኣገራችን ግልፅነትና ተጠያቂነት ስለሌለ በህዝብ ስም የሚሸቀጥባቸው ብዙ ፋብሪካዎእና የንግድ ማእከሎች ኣሉ። ለዚሁ እንደምሳሌ፤
የህወሓት መሪዎች በትግራይ ህዝብ ስም የሚነግዱበት በኣስር የሚቆጠሩ ፋብሪካዎች የንግድ ማእከሎች ግምታቸው እስከ 15 ቢልዮን በላይ ካፒታል ኣላቸው ይህ ካፒታል የውጭ ይሁን የውስጥ ግልፅ የሆነ ኦዲቶር የለውም ህዝብም በምንም ኣይነት የሚቆጣጠርበት መንገድ የለውም።እስኪ በህወሓት የሚወነኑ ፋብሪካዎችና የንግድ ማእከሎች ኣሉ።

1.ሲሚንቶ ፋብሪካ ካፒታሉ ከ4 ቢልዮን በላይ
2.ኣልመዳ ጨርቅ ፋብሪካ ከ3 ቢልዮን በላይ
3.ኣድዋ ጋርሜንት ከ600መቶ ሚልዮን በላይ
4.ኣዲ ግራት መድሃኒት ፋብሪካ ከ400 ሚልዮን በላይ
5.ሸባ ቆዳ ፋብሪካ ከ200 ሚልዮን በላይ ውቅሮ
6.ስጋ ፋብሪካ መሰቦ በመቶ ሚልዮን የተመሰረተ
7.ብሩህ ተስፋ ፕላስቲክ ፋብሪካ መቀለ በመቶ ሚልዮን የሚቆጠር የተቋቋመ
8.የሲሚንቶ ከረጢት ፋብሪካ በብዙ ሚልዮኖች የተቋቋመ
9.ችፑድ ፋብሪካ ማይጨው ከ250 ሚልዮን በላይ የተቋቋመ
10.ትራንስ ኢትዮጵያ በመቶ የሚቆጠሩ መኪናዎች ያሉት ከ1.5 ቢልዮን በላይ ካፒታል ያለው
11.መስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጅነሪንግ 2 ቢልዮን በላይ ካፒታል ያለው መቀለ ቃሊቲ ገርጅ
12.ኢዛና መኣድንና ወርቅ ፋብሪካ መቀለ መደባይ
13.ሂወት መካናይዜረሽን ከ500 ሚልዮን ካፒታል ህሞራ
14.ጥጥ መዳመጫ ዳንሻ በብዙ ሚልዮኖች የተቋቋመ
15.ደደቢት ብድርና ቁጠባ ከ4 ቢልዮን በላይ ካፒታል
16.ሜጋ ኮርፖሬሽን በስሩ ሜጋ ህትመት፣ሜጋ ኣከፋፋይ ፣ሜጋ ህንፃዎች
17.ሬድዮ ፋና ኣዲስ ኣበባ
18.ድምፅ ወያኔ ትግራይ
19.ጉለባል ኣሮጌ መኪኖች በኣገር ደረጃ የሚሸጥ
20.ወጋገን ባንክ ከ25 ቅርንጫፎች በላይ 51% የህወሓት
21.ኣፍሪካ ኢንሹራንስ ከ15 ቅርንጫፍ በላይ ከፍተኛ ሼር የያዘው
22.ጉና ኮርፖሬሽን፣መቀለ፣ኣዲስ ኣበባ፣ባህር ዳር፣ደሴ፣ህሞራ፣ሽሬ ቅርንጫፎች ከ 1 ቢልዮን በላይ ካፒታል
23.ሱር ኮንስትራክሽን ከ 1 ቢልዮን በላይ ካፒታል በየኣመቱ እስከ 2 ቢልዮን ኮንትራት የሚይዝ

24.ተከዜ የውሃ ቁፋሮ በብዙ ሚልዮኖች ካፒታል የተመሰረተ
25.ኢዛና የውሃ ቁፋሮ
ከላይ እንደዘረዘርኩት የትግራይ ህዝብ በክፉ ድህነት ምክንያት ወደ ስደት ተበታትነዋል ሴቶች በጣም ኣስከፊ የሆነ ስራ ተሰማርተዋል።የትግራይ ህዝብ በኣሁኑ ግዜ በመጥፎ ሁኔታ ኣለ።ታድያ የህወሓት ማ/ኮሚቴ በትክክል ለራሳቸው ዜጎች ከሆኑ የትግራይ ዜጎች ችግር ለመፍታት ያ በየኣመቱ የሚያተርፉት በቢልዮን የሚቆጠር ገንዘብ የትግራይ ወንዞች ተከዜም ጭምር ጎድጓዳ ቦታዎች በመገደብ መስኖ በመስፋፋት ህዝቡ ወደ ልማት ቢያስገቡት በሰው ምስጋናም በሰማይም ፅድቅ ያገኙ ነበር።በትግራይ እኮ ወርዒ፣ገረብ ግባ፣ሃይቅ መሰሓል፣ሱሉሕ፣ዓሬቋይ፣ዛምራ፣ፅላረ፣መረብ፣ሕርሚ፣ፍርፍራ ኣክሱም፣ፍርፍራ ፀለምት፣እብናት ፀለምት፣ኣቤራ ፀለምት፣ቡያ ፀለምት፣እንስያ ፀለምት፣ዛሬማ ወልቃይት፣ቃሌማ ወልቃይት፣ሱር ደደቢት፣ማይ ጤል፣ደደቢት፣ዊዳኸ ፣ኣድያቦ፣ምሲሓ መደባይ፣ተከዘ ራሱ በሌላ በእገላ፣ዕንጉያ በእገላ፣ሰቦሓ ሩባ በእገላ፣ፃዕደት በኣድዋ ወዘተ.ሊገደቡ ይችላል።እነዚህ ለመገደብ የህወሓት ኣመራር በየኣመቱ 2 ቢልዮን ገንዘብ ቢያወጣ በ5 ኣመት ውስጥ ለውጥ ያመጣ ነበር።ግን ኣንድ ጥርጣሬ ኣለኝ እንደ ቱኒዝያና ግብፅ መሪዎች ገንዘብ በተጠባባቂነት እያስቀመጡ እንዳይሆኑ! እኔ የምመክራችሁ የነዚያ በ17 ኣመት ፀረ ደርግ ትግል የተሰው ብዙ ሺ ታጋዮች ኣጥንት እንዳያንቀጠቅጥ እላችኋለሁ፥እና ለህሊናችሁ ስሩ።
ሌላ የህወሓት ኣመራር ኣቅጣጫ ተከትለው የሚሄዱ በህወሓት ሳንባ እየተነፈሱ የመጡና እየተነፈሱም ያሉ ብኣዴን፣ኦህዴድ፣ደህዴን በህዝብ ስም የሚሽቀጡባቸው ድርጅቶች ኣሉ።የነዚህ ሃብትም በመሬት ኢንቨስት ቢያደርጉት ያ በመፍረስ ያለ የጎጃም፣ጎንደር፣የወሎ፣የሸዋ፣የኦሮሞና የደቡብ ህዝቦች ወጣት ተሰዶ ከመሰቃየት በዳነ ነበር።
እንደኣብነት የብኣዴን በጥረት ስር የሚገኙ ድርጅቶች የማውቃቸው
1.ዘለቀ እርሻ መከናይዜሽን በመተማ
2.ቢራ ፋብሪካ በጎንደር
3.ጥቁር ኣባይ ትራንስፖርት
4.የኣማራ ልማት ማህበር
5.ኣንባሰል የንግድ ድርጅት ብዙ ቅርንጫፎች ያሉት
6.የኣማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም በቢልዮን የሚገባበት ካፒታል
እነዚህ ድርጅቶችም ገቢኣቸው በቢልዮን የሚቆጠር ሆነው ገቢኣቸውና ወጭኣቸው የኣማራ ህዝብ ኣያውቃቸውም።በኣማራ ህዝብ ድህነት ለማጥፋት መሰማራት ኣለባቸው።
ሌላ የዳንሾ የንግድ ድርጅቶች የደቡብ ወንዶ ድርጅት እንዳሏቸው ይታወቃል በዝርዝር ካፒታላቸው ባይታወቅም ኣሰራራቸው ግን ልክ እንድ

ኤፈርትና ጥረት  ግልፅነት ያልተከተለ አሰራር እንዳላቸው ነው የሚታሙት።ለነዚህ የምመክራቸው ህዝብ እንዲጠቀምበት ስራ ፈጣሪ እንዲሆኑ ሃሳቤን እለግሳለሁ።
የሚገርመው ነገር መንግስታችን በአሁኑ ግዜ ሴቶች ወጣቶች ከትግራይ ክልል ወደ አረብ አገር ልትሄዱ ፓስፖርት አውጡ ህክምና ተመርመሩ ቪዛ አስመትተን እንልካችኋለን እየተባሉ ለቪዛ 300 ብር ለምርመራ 350 ብር ለመጓጓዣ ጨምሮ በብዙ ሺ ገንዘብ እየከፈሉ በአስር ሺ የሚቆጠሩ ሴቶች እየመዘገበ ነው።ከሌሎች ክልሎችም እንደዚሁ እየተመዘገቡ ናቸው።ታድያ ህዝባችን ወደ ስደትና የከፋ ኑሮ ለመሄድ ከመደለል ይልቅ የፖለቲካ ድርጅቶች ንብረት የሆነ የኤፈርትና ጥረት ገንዘብ በትላልቅ ፕሮጀክቶች በማሰማራት ስራ ፈጥሮ ወጣቱ ወደዛ ቢያሰማራው መልካም አይሆንም?
የተከበራችሁ አንባብያን የኤፈርት ድርጅቶች እንዳየሁት የኢትዮድያ ህዝብ ይህ ሲያይ ትግራይ ልማት ብቻ ሳይሆን ትግራይ በልማት ሰመጠች ቢልም የተጋነነ አልነበረም ቢናገርም በሚያየው ነገር ነው።
ከላይ የተዘረዘሩትን የኤፈርት ድርጅቶች በየአመቱ ትርፋቸው የሁሉም በድምር በብዙ ቢልዮን የሚቆጠር ገንዘብ ነው እንደ አብነት የጥቂቶቹ የ2002ዓ.ም ትርፍ እናስቀምጥ።
1.ሲሚንቶ ፋብሪካ ግብር ከፍሎ ዲፕሪሼሽን ኮስት ቆርጦ የቫት ፣የሰራተኛና ሌሎች ተቆርጦ ከ1 ቢልዮን በላይ ትርፍ አግኝተዋል።
2.ትራንስ ኢትዮድያ ልክ እንደ ሲሚንቶ ፋብሪካ የሚቆረጥ ቆርጦ የ2002 ትርፍ 350 ሚልዮን በላይ አግኝተዋል።
ሌላ የኤፈርት ድርጅቶች በዚህ በ18 አመት ለህዝብ ያበረከቱ፥
1.በመቀሌ ከተማ ሃውዜን አደባባይና በካስትል አካባቢ ለተቀመጡት ቅርፃች መስርያ 11 መቶ ሺ
2.አካል ጉዳተኞች ህንፃ መስርያ 11 ሚልዮን
3.ለመሰቦ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ 17 ሚልዮን አውጥቷል።በተረፈ በዚህ 20 አመት ሙሉ አንድም ህዝባዊ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ተቋሞች አላሰራም።ያ ሁላ ትርፍ የት ገባ ለሚለው የህወሓት 45 ማ/ኮሚቴና ጠ/ሚኒስቴር መለስ፣አቶ ስብሓት ነጋ፣አቶ አርከበ ዕቁባይ፣አቶ ስዩም መስፍን፣አቶ አባዲ ዞሞ፣አዲስአለም ባሌማ፣ወይዘሮ አዜብ መስፍን ይመልሱት።
በዚች አገር ከታች ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ሚኒስቴሮች ደረጃ ሙሱና ተስፋፍቶ በየደረጃቸው ከሃብታሞች በመተሳሰርና በሚስጥረኝነት የአገሪቱ ሃብት በዝብዞውታል።ከዞን እስከ አዲስ አበባ ያሉ ከተሞች ከደምወዛቸውና ከገቢአቸው የማይመጣጠን ህንፃዎች ተሰርተዋል።ኑሮአቸው ፍፁም ከህብረተሰቡ የተለዩ ነው። በተለይ ከክልል አስተዳዳሪዎች ጀምሮ ሚንስትሮች ጦር ሞኮነኖች የቢሮ ሃላፊዎች ብዙ ህንፃዎች እየሰሩ

ለራሳቸው በመንግስት ቤት እየኖሩ በ10ሺዎች በ 100ሺዎች የቤት ኪራይ ያስገባሉ ዝርዝራቸው እና ጓደኞቻቸው በብዙ ሞቶ ሚሊዮን የሚገመት ሃብት ሰብስበዋል።

በአሁኑ ግዜ ባለስልጣኖች ሃብታቸው ያስመዝግቡ ተብሎ ንብረታቸውን ሲያዝመዘግቡ ይታያሉ ይህ ተግባር ድራማ ነው የሚመስለኝ 20 ዓመት ሙሉ ሃገሪቷን ከተመዘበረችና በቂ ገንዘብና ንብረት ካካበቱ አሁን መመዝገቡ ምን ማለት ነው? እስከ ዛሬ የወረርነው ሃብት ይቅር በሉልን ህጋዊነቱን አረጋግጡልን ነው የሚሉን ያሉት? በትክክል ሃቀኛ ምዝገባ ከሆነ እስከአሁን በራሱ በሚስቱ በልጆቹ በጓደኞቹ የተመዘገበ ንብረት ከየት መጣ ተብሎ መጠየቅ ነበረበት። በዚህ ቅርብ ጊዜ አንድ ነገር አየሁ ለስራ ጉዳይ ዩኤስ ኤ ሄጄ ነበር በተጨባጭ ያየሁት ነገር ቢኖር ቡዙ የመንግስት ባለስልጣኖች የዘመኑ ሃብታሞች ሚስቶቻቸውን ሲያረግዙ የመውለጃ ጊዚያቸው ሲቃረብ አሜሪካ ሄደው ይወልዳሉ ከወለዱ በኋላ አንዳንዶቹ ወዲያው ሲመለሱ አብዛኛዎቹ ግን እዛው ቀርተው ለአሜሪካ መንግስት ጥገኝነት ጠይቀው አዛው ይኖሯሉ ሌሎች ልጆቻቸው እና ዘመዳቸው ይወስዳሉ። ስራ ሳይሰሩ በምርጥ ቤቶች እየኖሩ ልጆቻቸውን በምርጥ ትምህርት ቤት ያስተምራሉ ባሎቻቸውም በየጊዜው ይመላለሳሉ። አንዳንድ ሃብታሞችም 2(3) ህንፃ ገዝተው ያከራያሉ ቤተሰቦቻቸውን ይኖርበታል ታድያ እንደዚህ ኣይነት ተግባር የሚፈፅሙ ሰዎች በትክክል ዜጎች ናቸው? በትክክል ለአገሪቱ ታማኝ ናቸው? ለምን አስቀድሞ ቤተሰቦቻቸውን ወደ አሜሪካ ይሸሻሉ?ምን ስለተጠረጣሩ ነው? ምናልባት የነግብፅና ቱኑዝያ እድል ቢያጋጥመን ሽሽተን መሸሸግያ ይሆነናል እና ተደበቀን እንደነ ካሳ ከበደና መንግስቱ ሃ/ማርያም ተደብቅን እንኖራልን ነው የሚሉን ያሉ? ታድያ እነዚህ ወራሪዎችና ጅቦች ይዘህ ነው የእድገት ትራንስፎርሜሽን እቅድ የሚሳካ እንዴት ብሎ ኣይታሰብም።

በሌላ በኩል በአሁኑ ግዜ የኢሃደግ ባለስልጣኖች ሚንስትሮች ልጆች በአሁኑ ግዜ በቻይና በለንደን በአሜሪካ ወዘተ የሚማሩ ያሉ ከሌሎች ዜጎች ተወዳድረው ነው የሚላኩት ያሉን ፍርዱ ለህዝብ ልተዎው?

ጤና በሚመለከት በአሁኑ ግዜ በደርግ እና በሃፀይ ሃይለስላሴ ያልነበሩ ሆስፒታሎች ክልኒኮች ጤና ጣብያዎች በ10ሺ የሚቆጠሩ ጤና ኬላዎች አሉ። ግን ይቅርና ጤና ኬላዎች እና ክሊንኮች ሆስፒታሎች ይቅርና ተራ በሽተኛ ሴቶች ምጥ ተይዘው ሆስፒታል ሲገቡ ቶሎ ብሎ ማከም ሳይሆን ሂድ ግላፕ ሻሽ መድሃኒት ወዘተ. ግዛ ነው የሚባለው። በአሁኑ ግዜ በ21ኛ ክ/ዘመን የከተማ ህዝብ ሳይቀር ወደ ጥንቆላ ፀበል ደብተራ የአበሻ መዳኒቶች ተመልሷል። ህክምና በሌለበት ጤናማ ዜጎች በሌሉበት ልማት ማለት ምንድነው? እንዴት ብሎ?

አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ በዚህ በክልላችን በሽሬ አውራጃ በታህታይ ቆራሮ ቀላቅል በተባለ ቀበሌ በፃእዳ ኣምባ ጎጥ ከአስር ኣመት በፊት ኣንድ

በሽታ ተከስቷል ያ በሽታ ሲጀምር መጀመርያ ብርድ ብርድ ይላል ቀጥሎ ሙቀት በመልቀቅ ያሳብዳል ሰውነትን ያቆስላል ሆድ ይነፋል ያብጣል። ኋላ የሆድ እቃው ጉበት ኩላሊት ኣንጀት ይቆስላል መጨረሻ በ3 እና 6ወር መካከል ያለው ጊዜ ያርፋል።በበሽታው የተለከፈ ኣይድንም ያበሽታው በኣንድ ፃእዳ እባ ጎጥ የጀመረ ኣሁን ተስፋፍቷል።እስካኣሁን እጅግ እጅግ ብዙ ሰው ኣልቋል በበሽታው ተለክፏል።ይግረማችሁ በ2001ዓ.ም ለትግራይ ክልል ጤና ቢሮ ኋላፊ ደጉተር ገብረኣብ ባርኖባስ የሪፖርተርና የኣዲስ ነገር ጋዜጣ ኣዘጋጆች ስለበሽታው ተጠይቀው ሲመልሱ በሽታው ወረኞች እንዲሚያጋንኑት ኣይደለም።በሽታው በፃእዳ እባ ጎጥ የተጀመረው ኣሁን ወደ 6 ወረዳዎቸ ተስፋፍቶ በፀለምት በታች ኣድያቦና በላይ ኣድያቦ በኣስገደ ፅምብላ በታች ቆራሮና ላኛው ቆራሮ ተከስቷል።ግን በሽታው ኣይተላለፍም እስከኣሁን የሞቱት 229 በበሽታው የተለከፉት 600 ናቸው ይላሉ ።ምን ማለት ነው ባመኑበት 229 ሰው ዝምብ ነው።በሽታው በኣሁኑ ግዜ በሺ የሚቆጠሩ ህዝቦች ተለክፏል።ስለዚህ በሽታ የመንግስት ብዙሃን መገናኛ ሽፋን ኣልሰጡትም።የትግራይ ክልል መሪዎች ይቅር የኣገር መሪዎች እንደዚህ ኣይነት እልቂት በስልጣን ኮረቻ ኣያስቀምጥም ነበር።በሌሎች ኣገሮች ሰው የሚከበርበት ከስልጣን ያስወርዳል።ይሀ ህዝብ ይዘህ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ለውጥ እንዴት ይመጣል።ላይ እንደጠቀስነው በኣገራችን ድህነት የወለደው ዝሙትና ሴተኛ ኣዳሪነት በዝቷል ከዛ ጋር በሽታው ተስፋፍቷል እንደዚህ ኣይነት ዜጋ ለውጥ ያመጣልን?ይህ ነው እድገት?በትምህርት በኩል የትምህርት ቤት ከኣንደኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ ጥራቱን በጣም ወርዷል።ለኣስተማሪዎች ብቃት ስልጠና ከመስጠት ይልቅ የኢህኣዴግ ኣባልነት ቅድሚያ በመስጠት ሁሉም መምህር በኢህኣዴግ ሳንባ ይተንፍስ ብቻ ሌላው ይቅር ተብሎ ተማሪዎችም ዋና መመዘኛቸው ኣባልነት ከሆነ ስለትምህርት ብዙዎችም ኣይጨነቁበትም።

ከዚህ የተነሳ የሚበዛ ተማሪ ከ8ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ይወድቃል 12ኛ ክፍል ኣልፎ ዩኒቨርሲቲ የገባም በግማሽ ኣመት ታፍሶ ወደ ቤቱ ይመለሳል።ያ ኣባልነት ኢህኣዴግ ተገን ኣድርጎ  በሞሞቅሞቅ ተመርቆ የወጣም ስራ ኣጥቶ ከላይ እንደተገለፀው በመጥፎ ቦታ እየተበላሸ ይገኛል በኣንፃሩም ዩኒቨርሲቲዎች ለፖለቲካዊ ማራመጃ እየተጠቀሙበት ነው ።ስለሆነ በኣገራችን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ሊመጣ ከሆነ የኢህኣዴግ መንግስት ውስጡን ፈትሾ ከላይ እስከ ታች ያለው መዋቅሩ ማፅዳትና ወጣቱ ህብረተሰብ ሙሁራኖች ሙያተኞች በመሳተፍ ለለውጥ መራመድ ኣለበት።ካለበለዝያ ለሸክም ኣሸጋሪዎች የሆኑ ይዞ የሚጓዝ ከሆነ የቱኒዝያና የግብፅ እድል ነው የሚጠብቀው።

አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የህወሓት ካድሬና የድርጅት ሃላፊ ሆነው የተመደቡ ዶክተር ይደግ አለማዮህ በግቢው የሚኖሩ አስተማሪዎችና ተማሪዎች የህወሓት አባል ካልሆንክ እያሉ ስጋት በመፍጠር በዩኒቨርሲቲው ህብረተሰብ ጭንቀት ይፈጥራሉ።ይህ እንደ ምሳሌ ለመጥቀስ ነው እንጅ፤

1.በሁሉም የአገራችን የኒቨርሲቲዎች ኮሌጆች የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የህወሓት፣ብአዴን፣ኦህዴድ፣ደህዴን ካደሬዎች ተወካዮች መቆጣጠርያ ፅ/ቤት አላቸው።ታድያ እነኚ ዩኒቨርሲቲዎች የምርምር ማእከሎች ናቸው ወይስ የፖለቲካ መራመጃ ናቸው?

ማሳሰብያ ለኢህአዴገ መንግስት

1.ከሁሉ በፊት መልካም አስተዳደር ነፃነትና ፍትህ በማስቀደም ሁሉም ኣይነት ሰብአዊ መብቶች በማስጠበቅ ግልፅነትና የህግ በላይነት ነፃ ዳኝነት ከሙስና የፀዳ ሆኖ ከሰራ ብቻ ሊኖር ይችላል።

2.የፖለቲካዊ ነፃነት ኑሮ የብዙሃን መገናኛ እኩል ተጠቃሚነት ኑሮ ነፃና ፍትሓዊ ታማኝ ምርጫ እንዲካሄድ ለማድረግ ከወገናውነት የፀዳ ምርጫ ቦርድና የምርጫ ህግ እንዲኖር ማድረግ ኣለበት ካልሆነ ዋዋ-----------------------------.

3.ባለስልጣኖች ሃብት መመዝገብ ከሆነ በ20 ኣመት ውስጥ ያካበቱት ሃብት ምንጩ ከየት መሆኑ መጣራት ኣለበት።

4.የኢትዮጵያ መንግስት መዋቅሩ በወጣቶችና በብቁ ሙሁራኖች ካልቀየረ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የሚባል ኣይመጣም ኣይታሰብም ።

5.ትምህርት ቤቶች ኮሌጆች ዩኒቨርሲቲዎች ኣስተማሪዎች በኢህአዴግ ሳንባ ካልተነፈሳችሁ ኣትኖሩም የሚል ቀርቶ ነፃነት ኖሮዋቸው ነፃ ሁነው ወደ ምርምር ሊገሰግሱ ይገባል ።

6.ኣድሎኣዊ የሆነ የውጭ የትምህርት እድል ያብቃ።በስልጣን ተገን በማድረግ ለባለስልጣኖች ልጆችና ቤተሰቦቻቸው የሚሰጥ የትምህርት እድል ኣብቅቶ በውድድርና ፍትሓዊ በሆነ መንገድ መፈፀም ኣለበት።

7.በኣሁኑ ግዜ የኢትዮጵያ ህዝብ ሙሁር ገበሬ ሳይለይ ወደ ስደት እየፈረሰና የተለያዩ ሃይሎች መሳርያ ሆኖ ኣገሪቱን እያደማ ነው።ለዚህ መንግስት ለተለያዩ ሃይሎች በመሰብሰብ ኣሳጥቆ እናት ኣገራቹ እንዲያደሙ የሚያደርገው የሻእብያ በርሃኛ ከምጥጩ መጥፋት ኣለበት ። ካለበለዝያ ከሻእብያ በመለማመጥ እና ሎሌ በመሆን በኣገራችን ልማትና የእድገት ትራንስፎርሜሽን ሊረጋገጥ ኣይችልም። የ ባህር በራችን ማስመለስ የግድ መሆን ኣለበት።

8. የህውሓት ኢሃደግ መንግስት በትክክል የቡዙሃን ፓርቲዎች(ማልቲ ፓርቲ) በኣገራችን መኖር ኣለባቸው ሰልጣን በውድድር መሆን ኣለበት የሚል እምነት ካለበት ለፖለቲካ ፓርቲዎች በድህንነት መዋከቡን ማሰር ማንገላታት ኣብቅቶ በሃሳብ በመከራከር በህዝብ ዳኝነት ነፃ ምርጫ ማመን

ኣለበት። በፓርቲዎች ሴራ መፈፀም ያቁም። እነዚህ ፓርቲዎች የሚሉት ማዳመጥ ኣለበት።
9. ፀረ ሙሰና የሚካየደው ዘመቻ ከስር ስሩ መሆን የለበትም ከጠቅላይ ሚንስተር ወለልና ጓሮ መጀመር ኣለበት ካለበለዝያ የምታደርጉት ፀረ ሙሰና እንቅቅስቃሴ ታማኝነት የለውም። ህዝብ እኮ ሁሉም ነገር ያውቃል በኣገራችን ያሉ የብድርና ቁጠባ ተቃማት ጥናት በጎደለው ለህዝቡ ያበደሩት ገንዘብ ለህዝብ ያፈረሰና ወደ ስደት ያዳረገ በመሆኑ እስካሁን የነበራቸውን እዳ ተሰርዞ ወደ ነበረበት እንዲመለስ ቢደረግ ኋላ በጥናት የተመሰረተ ቢበደሩ የተሻለ ይሆናል።
11. በትግራይ ያለው ኣስከፊ ድህንነት እና ስደት ሊቀረፍ ከሆነ የኢፈርት ገንዘብ በሙሉ ወደ ትላልቅ ግድቦች በማሰማራት ቡዙ ህዝብ በኣከባቢው ሊኖር በማድረግ መፍቲሄ ቢደረግለት
12. ከኢፈርት ድርጅቶች የህውሓት ኣመራር እጃቸው ኣውጥተው ህዝብ ራሱ ተረክቦ የመረጣቸውን ቦርድ ዳይርክተሮች እንዲመሩትና ያለፈው15ኣመት ወይ ከዛ በላይ ያተረፉት ገንዘብ በውስጥና በውጭ ኦዲተሮች ተረጋግጦ ለህዝብ ይፋ ሆኖ የሚጠየቁ ካሉ ይጠየቁ። የህዝብ ደምና ኣጥንት ነውና።
13. የ ኢፈርት ድርጅቶች ኣሁንም ለህዝብ ይካፈሉት የሚል ኣስተሳሰብ ካለ ድህነትን መካፈል ስለሆነ ኣሁን ባሉበት ሌሎች ተቃሞች እየፈጠሩ ድህነት ለማጥፋት ከላይ የተጠቀሱት ወንዞች በመገደብ ህዝብ በማስፈር ኑሮውን ማሻሻል ኣለበት።
14. የኣማራ ጥረትንና የኦሮሞ ድንሾ በህዝብ ቁጥጥር መዋል ኣለባቸው የሚል ኣስተያየት ኣለኝ።

*ይቀጥላል.....*

*ኣስገደ ገ/ስላሴ ወ/ሚኬኤል*
*ከ መቀሌ*
*ስ.ቁ 0344401144*
*0914757242*